# በበይነ መረብ መስመር ትምህርት (Online Learning) የከፍተኛ ትምህርት እውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር

### የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

ሐምሌ 2012
አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1. መግቢያ

ከፍተኛ ትምህርት ዘላቂነት ላለው የሰው ሀብት ልማት፣ ለቴክኖሎጂ አቅም ግንባታና ለሀገራዊ ዕድገት ያለውን ወሳኝ ሚና በመረዳት ሴክተሩ ታላላቅ የትምህርት ልማት ፕሮግራሞችን (ESDP I – V) በማዘጋጀት ሲተገብር ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም በሁለቱ ተከታታይ ሀገራዊው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶችም የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ አግባብነትና ጥራት ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት በርካታ ስኬቶች የተመዘገቡ መሆኑ ይታወሳል፡፡ በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ ላይ እንደተመላከተው ባለፉት ዓመታት የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች መጠነ ምዝገባ (enrolment rate) እና መጠነ ምረቃ (graduation rate) በሚፈለገው መጠን አለመሆኑ በ**2025** የታሰበውን **22%** ጥቅል የተማሪ ተሳትፎ ማድረስ አሳሳቢ እንደሚያደርገው ይጠቁማል፡፡

የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ የትምህርት ተደራሽነትን አስመልክቶ ኢትዮጵያ በ**2017** ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ከተቀመጡት ሪፎርሞች መካከል ጠንካራ የጥራት አጠባበቅ ስርዓት በመዘርጋት የትምህርትን ተደራሽነት ማሳደግ የሚለው ይገኝበታል፡፡ በመሆኑም በተለያየ ደረጃ የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትንና ፍትሀዊነትን ለማሳደግ፤ ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት የሚፈልጉ ተማሪዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ በመምጣቱና ይሄንን ፍላጎት በተለመደው መልኩ ተቋማትን በማስፋት ማርካት ስለሚያዳግት፤ ተቋማት በበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ከፍተኛ ትምህርትን መስጠት እንዲችሉ ሁኔታውን ማመቻቸትና አማራጭ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የአዋጅና የደንብ ማስፈጸሚያ መመሪያዎችን በማውጣት ሥራ ላይ ማዋል እንደሚችል እንዲሁም ኤጀንሲው የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትን እና ጥራትን ለማስጠበቅና የእውቅና ፈቃድና እድሳት አሰጣጥ መመሪያዎችንና የደረጃ መለኪያ መስፈርቶችን በማዘጋጀት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጥያቄ በመቀበል፣ በመገምገምና መሠረታዊ የሆኑ የጥራት መለኪያ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ዘርፉን በስርዓት እንደሚመራ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር **1152/2011** ያስቀምጣል፡፡ በመሆኑም ሚኒስትሩ በበይነ መረብ መስመር ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ የከፍተኛ ትምህርት ማስተማር ለሚፈልግ ተቋም የዕውቅና ፈቃድና የፈቃድ ዕድሳት ለመስጠት፤ በዚሁ አግባብ መከናወኑን ለመቆጣጠርና ጠንካራ የጥራት አጠባበቅ ስርዓት በመዘርጋት የበይነ መረብ መስመር ትምህርትን በተግባር ላይ ማዋሉን



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

ለመከታተል እንዲቻል ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አስፈላጊነት

ይህን መመሪያ ማዘጋጀት ያስፈለገው የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንጻር በዘርፉ የበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በመጠቀም ጥራትና አግባብነት ያለው የከፍተኛ ትምህርት እንዲሰጥ በማድረግ አገልግሎቱን ተደራሽና ፍትሀዊ ለማድረግ ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

በበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በመጀመሪያ፣ በሁለተኛና በሦስተኛ ዲግሪ ደረጃ ትምህርት ለማስተማር ለሚፈልግ ተቋም የእውቅና ፈቃድና እድሳት ለመስጠት፤ እንዲሁም በተደነገገው መስፈርት መሰረት መከናወኑን ክትትል፤ ድጋፍና ቁጥጥር ለማድረግ ነው፡፡

## 4. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ 'በበይነ መረብ መስመር (Online) የከፍተኛ ትምህርት እውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 806/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 5. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፦

5.1. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር **1152/2011** ነው፡፡

5.2. "ሚኒስቴር" ማለት የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ነው፡፡

5.3. "የከፍተኛ ትምህርት" ማለት በአዋጅ ቁጥር **1152/2011** አንቀጽ **2** ንዑስ አንቀጽ **8** የተመለከተውን ትርጉም ያመለክታል፡፡

5.4. "ኤጀንሲ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው፡፡

5.5. "ተቋም" ማለት የመንግስት ወይም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፡፡

5.6. "የዕውቅና ፈቃድ" ማለት በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የበይነ መረብ መስመር ትምህርት ለማስጀመር ለተቋም የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነው፡፡

5.7. "የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት" ማለት ቀደም ሲል በኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ ተሰጥቶት የፈቃድ ጊዜው ሲጠናቀቅ ተቋሙ ሥራውን እንዲቀጥል የሚሠጥ ፈቃድ ነው፡፡

5.8. “የማስተማሪያ መጽሐፍ” ማለት አንድን ትምህርት (ኮርስን) በበይነ መረብ መስመር ለማስተማር የሚረዳ ሰፋ ያለና ዝርዝር ይዘቶችን የያዘና ተማሪዎች በሚማሩበት ሙያ እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት እንዲጨብጡ የሚረዳ የዲጂታል ዶኩመንት (Digital learning materials) ነው።

5.9. “የማጣቀሻ መጽሐፍ” ማለት ሊሰጥ ለታሰበው ትምህርት (ኮርስ) ከማስተማሪያ መጽሀፍ የሚያገኟቸውን ትምህርት ለማጠናከር የሚያግዝ ተጨማሪ ማመሳከሪያና ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ዲጂታል መጽሐፍ ነው።

5.10. “ሳይንቲፊክ ጆርናል” ማለት ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶችና ሙያዊ ግምገማዎችና ትምህርታዊ ሃሳቦች የሚታተሙበት በዘርፉ ባለሙያዎች ተቀባይነት ያለው ዲጂታል ጆርናል ነው።

5.11. “መደበኛ ትምህርት” ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም (ከሰኞ እስከ ዓርብ) ውስጥ በስራ ቀናት በቀን ክፍለ-ጊዜ የሚሰጥ ትምህርት ነው።

5.12. “ቱተር” ማለት በበይነ መረብ መስመር ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ለሚማሩ ተማሪዎች በየደረጃው የአካዳሚክና ተዛማጅ ጉዳዮች ድጋፍ እና ተገቢውን ምክር የሚሰጥ መምህር ወይም የትምህርት ባለሙያ ነው።

5.13. “የበይነ መረብ መስመር ትምህርት (Online Learning)” ማለት ሙሉ በሙሉ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን በመጠቀም በበይነ መረብ አማካይነት ተማሪው በአካል በተቋሙ መገኘት ሳያስፈልገው ባለበት ቦታ ሁኖ ትምህርቱን እንዲከታተል በማድረግ የሚሰጥ የከፍተኛ ትምህርት ነው።

5.14. “ቅምራዊ ይዘት (Digital Content)” ማለት በበይነ መረብ መስመር የመማር ማስተማር ዘዴ በሥርዓተ ትምህርቱ መሠረት ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል ዲጂታል ይዘት ሕብረ ቅንብር ዲጂታል የማስተማሪያ ቁሳቁሶች (Multimedia Digital Learning Materials) የተዘጋጀ የትምህርት ይዘት ነው።

5.15. “የትምህርት አስተዳደር ስርዓት (Learning Management System)” ማለት በበይነ መረብ መስመር የመማር ማስተማር ዘዴ ትምህርት የሚሰጥበት ምህዳር ነው።

## 6. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የበይነ መረብ መስመር ትምህርት በሚሰጥ በማንኛውም ተቋም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# መሰረታዊ ጉዳዮች

## 7. መርሆዎች

በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ትምህርት ለመስጠት ተፈጻሚነት ያላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

7.1. የበይነ መረብ መስመር ትምህርቱ ከማንኛም የፖለቲካ አመለካከትና ከሃይማኖት ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ወይም “ሴኩላር” ነው፤

7.2. የቋንቋ ትምህርት ካልሆነ በስተቀር ለሁሉም ፕሮግራሞች ትምህርቱ የሚሰጥበት ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል፣

7.3. ማንኛውም ተቋም በተለየ ሁኔታ በህግ ካልተወሰነ በስተቀር ተማሪዎችን የሚቀበልበት ሥርዓት በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በልዩ ፍላጎትና በመደብ ልዩነት አይደረግበትም፤

7.4. ከኤጀንሲው በተሰጠ የእውቅና ፈቃድ አማካይነት በተለያየ መርሀ-ግብር በተመሳሳይ ደረጃ የተገኘ የትምህርት ማስረጃ እኩል ተቀባይነት ይኖረዋል፤

7.5. የበይነ መረብ መስመር ትምህርት የግምገማ ሥርዓት ህጋዊነትን፣ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ባሰፈነ መልኩ ይከናወናል፤

7.6. የዕውቅና ሥርዓት ከዓለምዓቀፍ ልምዶች የተቀመሩ አሠራሮችን፣ የሀገራችንን የከፍተኛ ትምህርት ዕድገት ደረጃን ያገናዘበና በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ እንዲሆን ይደረጋል፤

7.7. የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥ ተቋማት ያላቸውን የትምህርት ግብዓት በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 8. ተቋም ስለማቋቋምና የዕውቅና ፈቃድ ጥያቄ ስለማቅረብ

### 8.1. ተቋም ስለማቋቋም

8.1.1. የሚቋቋመው ተቋም ሀገራዊና ሕዝባዊ ፍላጎቶችን ማዕከል ያደረገ አላማ፣ ርዕይና ተልእኮ ሊኖረው ይገባል፤

8.1.2. ተቋሙ የሚቋቋመው በአክሲዮን ወይም በግል (ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር) ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ፤ እንዲሁም የተቋሙን ህጋዊ ባለቤትነት የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

8.1.3. አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችለውን የኢንቨስትመንት እና የንግድ ምዝገባ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርበታል፤

8.1.4. ተቋሙ በቀጣይ ጊዜያት ለመስራት ያቀዳቸውን ስራዎች የሚያሳይ የ5 ዓመት ስልታዊ (ስትራቴጂክ) እቅድ ማቅረብ አለበት፤

8.1.5. ተቋሙ ለሥራው የማይንቀሳቀስ ዋስትና በገንዘብ ብር **500,000.00** (አምስት መቶ ሺህ) በባንክ ማስያዝ ወይም ተመጣጣኝ የባንክ ዋስትና ማቅረብ አለበት፤

8.1.6. ከዚህ በፊት በስራ ላይ ቆይተው በበይነ መረብ መስመር ትምህርት የእውቅና ፈቃድ ለሚጠይቁ ተቋማት ለመርሃ ግበሩ የሚያስፈልጉትን የሰው ሃይል እና ግብአት በመገምገም ጥያቄያቸው የሚስተናገድ ይሆናል።

8.1.7. የመንግስት ተቋም ማቋቋምን በተመለከተ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር **1152/2011** አንቀጽ **5** መሰረት የሚታይ ይሆናል::

## 8.2. **ዕውቅና ፈቃድ ጥያቄ ስለማቅረብ**

በአዋጅ ቁጥር **1152/2011** አንቀጽ **73** ንዑስ አንቀጽ **1**፣ **2** እና **3** ላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ተቋም ለመክፈት ወይም አዲስ መርሃ-ግብርና የትምህርት መስክ ለመክፈት ወይም በተፈቀደለት ፕሮግራም የተማሪ ቅበላ መጠን ለማሳደግ የሚፈልግ ማንኛውም ተቋም የሚያቀርበው የእውቅና ጥያቄ ማመልከቻ፣ የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ አለበት::

8.2.1. የተቋም ስምና ዋና አድራሻ፤

8.2.2. እውቅና የተጠየቀበት ከተማና የቦታው ልዩ መጠሪያ፤

8.2.3. የእውቅና ጥያቄ የቀረበበት ትምህርት ደረጃ፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት ዘዴ (መርሃ-ግብር) እና የትምህርት መስክ፤

8.2.4. በእያንዳንዱ የትምህርት መስክ በዓመት ሊቀበል የሚችለው የተማሪ መጠን፤

8.2.5. የተቋሙ ተጠሪ የሆነ አካል ስምና አድራሻ፣

8.2.6. የተቋሙን ባለቤትነት (ህጋዊ ሰውነት) ማረጋገጫ ማስረጃ ሰነድ፤ የተቋሙን ባለቤቶች ስምና አድራሻ፤ በሚገልጽ መልኩ ማህተም ተደርጎበት መቅረብ ይኖርበታል።

8.2.7.የተቋሙ አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀት፣

8.2.8. ተቋሙ ለሚያቀርበው የደረጃ ስያሜ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችና መረጃዎች፣

8.2.9. የኤጀንሲውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና በቅፁ ላይ የተመለከቱት ግብዓቶች መሟላታቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች፣

8.2.10. ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት በየመረሀ-ግብሩ ለማመልከት አስፈላጊ የሆኑትን የአሰራር ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች ፣

8.2.11. በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችል የንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የንግድ ምዝገባ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

8.2.12. ለኦንላይን ትምሕርት ለመጀመር አስፈላጊ ከሆኑት ዋናዎቹ፤ Website, data centre and dedicated server (24/7) standard Learning Management System (including online registraion and E-Payment system), studios for online lesson production, complete digital learnming courses (maeterials) for all study fields, informaiton security system. ማቅረብ፣

8.2.13. የሕንጻ የይዞታ ማስረጃ ወይም ለ3 ዓመት የሚያገለግል የኪራይ ውል፣ እና

8.2.14. ለእውቅና ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ ማስረጃ::

## 8.3. የዕውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ስለማቅረብ

በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ትምህርት ሲሰጥ የቆየ ተቋም የትምህርት መስኩን ለመቀጠል አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ማመልከቻ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት። ማመልከቻው በክፍል ሶስት አንቀጽ 7 የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

8.3.1. የትምህርት ግብዓቶችና መገልገያዎች እየተሟሉና እድገት ያለ መሆኑን የሚያሳይ ሪፖርት፤

8.3.2. የተቋሙ የአካዳሚክ፣ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት እንዲሁም የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ከነሙያዊ ዳራቸውና ደረጃቸው ጋር የሚያሳይ ዝርዝር፤

8.3.3. በየዓመቱ ተቋሙ በሚሰጠው በእያንዳንዱ የትምህርት መስክ የተመዘገቡ ተማሪዎች ዝርዝር፤

8.3.4. በውጭ ኦዲተር የተመረመሩ የመጨረሻዎቹን ሁለት ዓመታት የሂሳብ ሪፖርቶች፤

8.3.5. ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት፤

8.3.6. እውቅና ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ የተደረጉ ማሻሻያዎች እና የመማር ማስተማር ሂደቱን እና መሠረታዊ የዲጂታል መሰረተ ልማት ተደራሽነትነ ለማሳደግ የተደረጉ ጉልህ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ሪፖርትና ማስረጃ፤

8.3.7. ተቋሙ ካለው የፕሮግራሞች ዓይነት አኳያ ለትምህርት ጥራት መሻሻል በያዘው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ መሰረት መዋእለንዋይ እያፈሰሰ መሆኑን የሚያሳይ የጥራት ማጎልበት ተግባር እና የምርምርና ስርፀት የሥራ ክንውን ዓመታዊ ሪፖርት፤

8.3.8. በተቋሙ ላይ በማህበረሰቡ፣ በመምህራንና በተማሪዎች የቀረበ ቅሬታንና የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃን የያዘ ሪፖርት፣ እና

8.3.9. ተቋሙ የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን የሚያሳይ አመታዊ ሪፖርትና ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

8.3.10. የትምሕርት አሰጣጥ መርሁ የተጣመረ ትምህርት (Blended Learning) የተከተለ ከሆነ፤ ዋና የትምሕርት አሰጣጥ በበይነ መረብ መስመር ሆኖ፤ ነገር ግን ሴሚናሮች፤ ፈተናዎች፤ የላቦራቶሪ ሙከራዎችና የመሳሰሉት በመደበኛ ፊት ለፊት የመማር ማስተማር ዘዴ ሊደገፉ የችላሉ፡፡ ነገር ግን ከጠቅላላ ትምሕርቱ በበይነ መረብ መስመር የሚሰጠው ከ **60** ከመቶ ማነስ የለበትም፡፡

## ክፍል ሦስት
## የዕውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

### 9. የመገምገሚያ መስፈርቶች

በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት በበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ትምህርት ለመስጠት የተዘጋጀ ተቋም ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር የሚችለው የሚከተሉት መሠረታዊ የጥራት መለኪያ መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ስለመሟላታቸው በኤጀንሲው ሲረጋገጥና የእውቅና ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ ነው።

#### 9.1. ህንጻና አካባቢያዊ ሁኔታ

9.1.1. ተቋሙ የሚጠቀምበት ህንፃ በስሙ የተመዘገበ ስለመሆኑ የባለቤትነት ሰነድ ወይም ተቋሙ የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ለ3 ዓመታት ማገልገል ስለማስቻሉ በሕግ ፊት የጸና የኪራይ ውል ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፤

9.1.2. ተቋሙ በአንድ ህንፃ ወለል ላይ ተከራይቶ ትምህርት የሚሰጥ ከሆነ በተከራየው የህንፃ ወለል ላይ ሌሎች የንግድ ተቋማት ተቋሙ በተከራየው ክፍሎች መሀል ሊኖሩ አይገባም፤

9.1.3. ተቋሙ ያለበት አካባቢያዊ ሁኔታ ለበይነ መረብ መስመር ትምህርት ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹና የመሬቱ አቀማመጡ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ያልተጋለጠ ሊሆን ይገባል፤

9.1.4. ተቋሙ የሚጠቀምበት ህንፃ አስፈላጊ አገልግሎቶች ማለትም መብራት፣ መብራት በማይኖርበት ወቅት አገልግሎት የሚሰጥ ዘላቂ ጀኔሬተር፣ ውሃና የኢንተርኔት አገልግሎት ሊኖረው ይገባል፤

9.1.5. ተቋሙ የሚጠቀምበት ህንፃ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዝርጋታ (IT infrastructures installation) እና በቂ ባንድ ዊድዝ ሊያሟላ ይገባል፣

9.1.6. ተቋሙ የሚጠቀምበት ህንፃ ለተቋሙ ሠራተኞችና እንግዶች አገልግሎት የሚሰጡ በቂ የመጸዳጃ ክፍሎች፣ የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና እርዳታ መስጫ እና የመዝናኛ ክበብ ወይም የመዝናኛ አገልግሎት ሊኖረው ይገባል።

## 9.2. አመራርና አደረጃጀት

9.2.1. ተቋሙ በበይነ መረብ መስመር የቴክኖሎጂ ትምህርት ለመስጠት የሚያስችለው ግልጽና አስፈላጊውንተቋማዊ መዋቅርና የሰው ሃይል ሊኖረው ይገባል:: ተቋማዊ መዋቅሩም የተቋሙ ኃላፊ፣ የትምህርት ክፍል አስተባባሪዎች፣ የቅምራዊ ይዘት ዝግጅት ክፍል አስተባባሪ፣ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ አስተዳዳሪ፣ የምዘናና የፈተና ክፍል ኃላፊ፣ የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት (Technical support) ኃላፊ፣ የውስጥ ጥራት ማረጋገጥ አገልግሎት ኃላፊ፣ የጥናትና ምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ኃላፊ፣ ሬጅስትራርንና የአስተዳደር አገልግሎት ኃላፊን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፤

9.2.2. የተዘጋጀው ተቋማዊ መዋቅር የተቋሙን የበላይ ወሳኝ አካልን (ሴኔት ወይም አካዳሚክ ካውንስል)፣ ቋሚ ካውንስሎችንና ኮሚቴዎችን ጨምሮ ሌሎች የሥራ ክፍሎች ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ባመላከተ መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፤

9.2.3. በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ለማስተማር የሚፈልግ ተቋም፣ የተቋሙ ኃላፊ ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያለው እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በማስተማር ቢያንስ ስድስት ዓመት ወይም በአመራርነት ቢያንስ የአራት ዓመት ልምድ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ በተጨማሪም የትምህርት ክፍል አስተባባሪዎች በትምህርት መስኩ ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያላቸውና በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ስልጠና የወሰዱ ወይንም ልምድ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፤

9.2.4. በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ለማስተማር የሚፈልግ ተቋም የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ አስተዳዳሪ፣ ዋና ሬጅስትራር፣ የምዘናና ፈተና የሥራ ክፍል ኃላፊ፣ የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት (Technical support) ኃላፊ፣ የጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ክፍል ኃላፊ እና የጥራት ማረጋገጥ ሥራ ክፍል ኃላፊ ለየሥራ ኃላፊነታቸው ተመሳሳይነት ባለው የሥራ መስክ ቢያንስ የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው እና ለየሥራ መስኩ አግባብነት ባለው የትምህርት መስክ ቢያንስ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የተመረቁ ሊሆኑ ይገባል፤

9.2.5. ከማስተርስ ዲግሪና ከዚያም በላይ ለማስተማር የሚፈልግ ተቋም ኃላፊ ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት አካዳሚክ ማእረግ ያለውና በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በማስተማር ቢያንስ ስምንት ዓመት ወይም በአመራርነት ቢያንስ ስድስት ዓመት ልምድ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ በተጨማሪም የትምህርት ክፍል አስተባባሪዎች ሁለተኛ ዲግሪ ለሚያስተምር ተቋም በትምህርት

መስኩ ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት አካዳሚክ ማእረግ ያላቸውና ሦስተኛ ዲግሪ ለሚያስተምር ተቋም በትምህርት መስኩ ቢያንስ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት አካዳሚክ ማእረግ ያላቸውና በበይነ መረብ መስመር ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ስልጠና የወሰዱ ወይም ልምድ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፤

9.2.6. በማስተርስ ዲግሪና ከዚያ በላይ ለማስተማር የሚፈልግ ተቋም የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ አስተዳዳሪ፣ የሬጅስትራር ኃላፊ፣ የምዘናና ፈተና የሥራ ክፍል ኃላፊ፣ የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት ኃላፊ፣ የጥናትና ምርምር እና የጥራት ማረጋገጥ ሥራ ክፍል ኃላፊዎች ለየሥራ ኃላፊነታቸው ተመሳሳይነት ባለው የሥራ መስክ ቢያንስ የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው እና ለየሥራ መስኩ አግባብነት ባለው የትምህርት መስክ ቢያንስ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የተመረቁ ሊሆኑ ይገባል፤

9.2.7. የተቋሙ ሰራተኞች የሥራ ድርሻቸው (መዘርዝር) በጽሑፍ በተደገፈ ሰነድ አደራጅቶ ሊሰጣቸው ይገባል፤ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ብቃትን መሰረት ባደረገ ውድድር ለመመልመል፣ ለማሰደግና አስተዳደራዊ ማስተካከያዎችን ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤

## 9.3. **ስርዓተ ትምህርት**

9.3.1. ተቋሙ የስርዓተ ትምህርት አዘገጃጀት፣ አተገባበር፣ ግምገማና ክለሳ የሚከታተልና ግብረመልሶችን በመሰብሰብ በቀጣይነት የሚያሻሽል ተገቢ አደረጃጀትና ስርዓት ሊኖረው ይገባል፤

9.3.2. ስርዓተ ትምህርቱ ከአገር ፍላጎት ጋር የተገናዘበ፣ አግባብነት ያለው፣ ሚዛናዊ እውቀትን፣ በተግባር የሚተረጎም ክህሎትን፣ የበሰለ ስብዕናን፣ የጠነከረ ማህበራዊ እሴቶችንና የጠለቀ አስተሳሰብን የሚያላብስ፣ ተማሪዎቹን ለሥራ የሚያዘጋጅና ችግር ፈቺ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆኑን በሚያረጋግጥ ሁኔታ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፣ በአውደ ጥናት የተደገፈና የባለድርሻዎችን አስተያየት ባካተተ መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፤

9.3.3. በበይነ መረብ መስመር የሚሰጠው ስርዓተ ትምህርት ይዘት በወቅቱ በዘመነ የበይነ መረብና በሌሎች አጋዥ ቴክኖሎጂዎች፣ አመችና ለመማር በቀለለ መንገድ (Modularized) የተደራጀና እየዳበረ መሄድ ያለበት በመሆኑ ቢያንስ በ3ዓመት አንድ ጊዜ መገምገም አለበት፤ ከዚህ የሚገኘው ውጤትም ስርዓተ ትምህርቱን ለማሻሻል መዋል አለበት፤

9.4.2. ድምጽን የማያሳልፍ የሆነና አስፈላጊ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂዎችና ሶፍትዌሮች የተሟሉለት የሪኮርዲንግ ስቱዲዮ (Multimedia development) ማደራጀት ይኖርበታል፤

9.4.3. ቅምራዊ ይዘት ለማዘጋጀትና በቀጣይነት ለማሻሻል ብቃትና ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎችን ለመመልመል የሚያስችለው ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤

9.4.4. ቅምራዊ ይዘት በሚዘጋጅበት ወቅት ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚደረግ የማቴሪያል አጠቃቀምን፣ የተዘጋጁትን ኮርሶችንም ሆነ ይዘቶች የባለቤትነት መብትን (Copy right / intelectual property right) በጠበቀና ስርቆትን (plagiarism) በሚከላከል አግባብ ሊከናወን ስለሚችልበት ሁኔታ ተቀባይነት ያለው የአጠቃቀም ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል፤

9.4.5. ተቋሙ የእያንዳንዱ ኮርስ ይዘት መመሪያን ወይም ማንዋልን በተከተለ መልኩ ቅምራዊ ይዘት የማዘጋጀት ልምድ ካላቸው ወይንም ስልጠና ከወሰዱና ለመጀመሪያ ዲግሪ ቢያንስ በትምህርት መስኩ በማስተርስ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ካላቸው፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት የአካዳሚክ ማዕርግ ደረጃ ካላቸው እንዲሁም ለሦስተኛ ዲግሪ ቢያንስ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ደረጃ ካላቸው መምህራን ጋር ሊያሰራው የሚችል የስምምነት ውል ሊገባ ይገባል፣

9.4.6. ቅምራዊ ይዘት በሚዘጋጅበት ወቅት የትምህርት መስኩ ባለሙያ፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት ቋንቋ ባለሙያ፣ የስርዓተ ትምህርት ባለሙያ (Multimedia development)፣ የግራፊክስ ቪዲዮ፣ አኒሜሽን፤ ሲሙሌሽን ዲዛይነር፣ ይዘት ናሬሽን ባለሙያ፣ ኤዲተሮች እና የአይሲቲ ባለሙያዎች ሊሳተፉ ይገባል፤

9.4.7. በስርዓተ ትምህርቱ የኮርስ ክፍፍል መሰረት ለእያንዳንዱ የትምርት ኮርስ ለተመደበው የትምህርት ግዚያት/ዓመታት አገልግሎት የሚሰጡ ቅምራዊ ይዘቶች ሊዘጋጁ ይገባል፣

9.4.8. ቅምራዊ ይዘቱ የትምህርት መስኩ የሚፈልገውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ያካተተ ምክንያታዊነት፣ አሰላሳሊነትንና የመፍትሄ ሃሳብ ፈጠራን በሚያበረታታ መልኩ የሚዘጋጁና ልዩ እገዛ የሚሹ ዜጎችን ያማከለ ሊሆን ይገባል፤

9.4.9. ቅምራዊ ይዘቱ ከሥርዓተ-ትምህርቱ ጋር በተጣጣመና የተለያዩ የተማሪ አቅምን፣ ደረጃንና ፍላጎቶችን ባካተተ መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፤

9.4.10. ቅምራዊ ይዘቱ በምእራፎች ማብቂያ ላይ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲገመግሙ የሚያስችላቸው መልመጃዎች ሊኖሩት ይገባል፤

9.4.11. በቅምራዊ ይዘቱ የኮርስ ግምገማና ድጋፍ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል። በበይነ መረብ መስመር የሚሰጠው ኮርስ ይዘት፣ በአዲስ ቴክኖሎጂና የኮርስ አቀራረፅ ስፋት የዳበረ ስለመሆኑ ቢያንስ በ2 ዓመት አንድ ጊዜ መገምገም አለበት፤ ከዚህ የሚገኘው ውጤት ኮርሱን ለማሻሻል መዋል አለበት፤

9.4.12. ቅምራዊ ይዘቱ በትምህርት አስተዳደር ስርዓት ጥቅም ላይ ከመዋሉ በተጨማሪ የተማሪዎችን ተጨማሪ ፍላጎት ለማርካት በተለያየ መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፤

9.4.13. ተቋሙ የኮርስ አካሄድንና አስተዳደርን በተመለከተ ለተማሪዎች፣ ለኮርሱ መምህርና ለፕሮግራሙ አስተባባሪ ተገቢውን ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

9.4.14. የቅምራዊ ይዘቱ በሚዘጋጅበት ወቅት በተማሪና መምህር እንዲሁም በተማሪና ተማሪ መካከል ተግባቦት መኖሩን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ሊያካትት ይገባል።

## 9.5. የትምህርት አስተዳደር ስርዓት (Learning Management System) እና የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ (e-learning platform)

9.5.1. የተቋሙ የትምህርት አስተዳደር ስርዓትና ሌሎች አገልግሎት የሚሰጥባቸዉ የቴክኖሎጂ ግብአቶችና መሰረተልማቶችን የሚያስቀምጠው (host) የዳታ ቤዝ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (Public Cloud) ላይ ከሆነ የሚያገኘው አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ ከአገልግሎት ሰጪው ተቋም ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፣ ነገር ግን ተቋሙ የራሱን ዳታ ቤዝ የሚጠቀም ከሆነ ቢያንስ የኔትዎርክ፣ የዳታ ማእከልና የአፕሊኬሽን የደህንነት ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፤

9.5.2. ተቋሙ አገልግሎት የሚሰጥባቸዉ የቴክኖሎጂ አፕሊኬሽኖችና መሰረተልማቶች በራሱ ዳታ ማእከል (Premises) የሚጠቀም (host) የሚያደርግ ከሆነ ቢያንስ 512 Kbps ለአንድ ተማሪ ምጣኔ አቅም ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት ሊኖረው ይገባል፤

9.5.3. ተቋሙ ደረጃውን የጠበቀ በይነ-መረብ (website) ሊኖረውና የሚያገኘው የኢንተርኔት አገልግሎት ቢያንስ 8 ሜጋ ባይት በሰከንድ ለ1000 (አንድ ሽህ ተማሪ) ምጣኔ የኢንተርኔት አቅም ሊኖረው ይገባል፤

9.5.4. በተዘጋጀው ትምህርት አስተዳደር ስርዓቱ ላይ ስለሚደረጉ ውይይቶችና ግንኙነቶች አጠባበቅ፣ የውስጥ የመረጃ ልውውጥ ህግጋትና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተቋሙ አቋም በዝርዝር ፖሊሲ ሊዘጋጅ ይገባል፤

9.5.5. ለትምህርት አስተዳደር ስርዓቱና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎት የሚሰጡ የአይሲቲ መሰረተልማቶቹ በሳምንት 7 ቀናት ለ24 ሰዓታት አገልግሎት የሚሰጥና በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን በሙሉ ማካተት ይኖርበታል፤ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር የተዘረጋው ስርዓት የማይሰራበት ሁኔታ ቢፈጠር ተቋሙ ተማሪዎች ትምህርት ሊቀጥሉ የሚችሉበትን አማራጭ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤

9.5.6. ለትምህርት አስተዳደር ስርዓቱ ከትምህርት መስኩ ጋር አግባብነት ያላቸውን በቅርብ ጊዜ (በ10 ዓመት ውስጥ) በታተሙ የዲጂታል (ኤሊክትሮኒክ) የመማሪያና የማጣቀሻ መጻሕፍት፣ ቅምራዊ ይዘትና ሳይንሳዊ ጆርናሎች ሊያደራጅ ይገባል፤

9.5.7. ለትምህርት አስተዳደር ስርዓት የተቀመጠው ኦሪጅናል ቅምራዊ ይዘት በማይቀየርበት አግባብ ለመምህሩ ለተማሪዎች ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት እንዲያስችለው ኮንቴንቱ ላይ የመጨመር፣ ሌሎች አስፈላጊ ጥቅሞችን እንዲሰጥ ሊፈቅድለት ይገባል፤ ለተማሪዎችም የሚፈልጉትን ሪሶርስ እንዲያገኙ ሊያስችላቸውና ለአጠቃቀም ቀላል ሊሆንላቸው ይገባል፤

9.5.8. ለትምህርት አስተዳደር ስርዓቱ በቀጥታ (Video Conferening) ትምህርት ሊሰጥ የሚያስችል አገልግሎት ሊኖረው ይገባል። በዚሁ መሰረት ኮርሱ ባለ 1 እና 2 ክሬዲት አወር ከሆነ 2 ጊዜ፤ ኮርሱ ባለ 3 ክሬዲት አወር ከሆነ 3 ጊዜ፤ ኮርሱ ባለ 4ና ከዛ በላይ ክሬዲት አወር ከሆነ 4 ጊዜ እኩል በተከፈሉ ወቅቶች ተማሪዎች ከቱተሮች ጋር የሚገናኙበት በአንዱ ግንኙነት ወቅት ከ2 ሰዓት ርዝማኔ ያላነሰ የቀጥታ (live) ትምህርት አገልግሎት ሊኖር ይገባል፤

9.5.9. ተማሪዎች በቀጥታ (Video Conferening) ፕሮግራሞቹን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስለመሳተፋቸው የሚከታተልበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤ እንዲሁም የቀጥታ (live) አገልግሎት ፕሮግራም በተለያየ ችግር ላልተከታተሉ ተማሪዎች ፕሮግራሙ ተቀርጾ የሚቀርብበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል፤

9.5.10. ለትምህርት አስተዳደር ስርዓቱ ካሌንድር፡ ለተማሪዎች፤ ዲጂታል ኮርሶችንና ተጨማሪ የንባብ

ማጣቀሻዎችን፤ የመወያያና ሐሳብ መለዋወጫ ሥርዓት (Synchronous and Asynchronous Discussion Board)፣ ኢሜል፣ ፈተና ውጤት ማሳያ፤ ተማሪዎች የቤት ሥራዎቻቸውን፤ ፕሮጀክቶችንና የምርምር ውጤቶችን የሚያስረክቡበት፡ ያካተተ ሊሆን ይገባዋል፡

9.5.11. ተቋሙ ሁለተኛ ዲግሪና ከዚያም በላይ እውቅና ለጠየቀባቸው የትምህርት መስኮች አግባብነት ያላቸውን ሳይንቲፊክ ጆርናሎች ተደራሽ ሊያደርግ የሚያስችል ዓለም አቀፍ በይነ መረብ መስመር በቀጣይነት ሊያገኝ በሚችልበት አግባብ ታዋቂ ጆርናሎች ሊኖረውና ለተማሪዎች አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት ሁኔታ ሊያደራጅ ይገባል፤

## 9.6. **የመምህራንና የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት**

9.6.1. አንቀጽ 9.2. ስር ስለ ትምህርት መስክ አስተባባሪዎች የተቀመጠው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተቋሙ በቋሚነት ከቀጠራቸው የትምህርት መስክ አስተባባሪዎች በተጨማሪም የ20% ቋሚ 80% ጊዜያዊ ጥመርታ መምህራን ሊኖረው ይገባል፤

9.6.2. ተቋሙ የመምህራን መመልመያ ማንዋል ስለማዘጋጀቱና በተዘጋጀው የመመልመያ መስፈርት መሰረት ቢያንስ ለ100 ተማሪ አንድ መምህር ምጣኔ መሰረት መምረጥና አስፈላጊ የቅጥር ሂደቶችን ማሟላት ይኖርበታል፤

9.6.3. ለእያንዳንዱ የትምህርት መስክ በበይነ መረብ መስመር ትምህርት አገልግሎት የሚያስተምር መምህር ቢያንስ ከሚያስተምረው የትምህርት ደረጃ አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ የሚገኝ ሊሆን ይገባል፤ የመጀመሪያ ዲግሪ የሚያስተምሩ መምህራን በትምህርት መስኩ ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው፣ የሁለተኛ ዲግሪ የሚያስተምሩ መምህራን በትምህርት መስኩ ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት አካዳሚክ ማእረግ ያላቸውና ሦስተኛ ዲግሪ የሚያስተምሩ መምህራን በትምህርት መስኩ ቢያንስ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት አካዳሚክ ማእረግ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፤

9.6.4. ቋሚና ተጋባዥ መምህራን በበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ፣ ትምህርት አስተዳደር ስርዓት (LMS) አሰራርና ቅምራዊ ይዘት አጠቃቀም ላይ ተገቢ ስልጠና የወሰዱ መሆን አለባቸው፤

9.6.5. መምህራኑ ከመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያም በላይ ያሏቸው የትምህርት ማስረጃዎቻቸው

ከነትራንስክሪፕታቸው፣ የቅጥር ደብዳቤ እና ከተቋሙ ጋር የገቡት የስራ ስምምነት ውል ለኤጀንሲው መቅረብ ይኖርበታል፤

9.6.6. ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተገኘ የመምህራን የትምህርት ማስረጃ በኤጀንሲው የአቻ ግመታ የተሠራለት መሆን አለበት፤

9.6.7. የመምህራን የሙያ ስልጠና በየደረጃው የሚያሣየው ተመሣሣይ መሆን ያለበት ሲሆን ከሚያስተምሩት የትምህርት መስክ (digital pedagogy) አንጻር በተዘጋጀና ተቀራራቢ የትምህርት ዘርፍ አንጻር የሚታይ ይሆናል፤

9.6.8. የመመረቂያ ጽሑፍ ላይ ሊያማክሩ የሚችሉ ለሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ከረዳት ፕሮፌሰርና ከዚያ በላይ የአካዳሚክ ማዕረግ ካላቸው መምህራን ጋር 1፡8 ጥመርታ እንዲሁም ለሦስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ከተባባሪ ፕሮፌሰርና ከዚያ በላይ የአካዳሚክ ማእረግ ካላቸው መምህራን ጋር 1፡3 ጥመርታ መሰረት የስራ ውል ሊታሰር ይገባል፤

9.6.9. ተቋሙ ተማሪዎችን በበይነ መረብ መስመር የማማከር ስርዓት ሊኖረው ይገባል፣

9.6.10. ተቋሙ ተማሪዎች በሚገጥሟቸው ቴክኒካዊና ማህበራዊ ችግሮች ዙሪያ በቀጣይነት ድጋፍ ሊያገኙ የሚያስችላቸውን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤

9.6.11. የተቋሙ የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት ክፍል በኮል ሴንተር (call center) ከጀርባ የቢሮ አገልግሎት (back office support) አግባብነት ባላቸው ባለሙያዎች ሊያደራጅ ይገባል፤

9.6.12. የተቋሙ የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት ተማሪዎች የገጠማቸውን ችግር ሊረዳ የሚያስችለውን ምቹ የመረጃ መቀበያ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤

9.6.13. የተቋሙ የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት ተማሪዎች በትምህርት አስተዳደር ስርዓትና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ የተማሪዎችን ችግር በመለየት ድጋፍ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፤

9.6.14. መምህራን ለተማሪዎች ሊሰጥ የሚገባውን ቴክኒካዊ እርዳታና ድጋፍ በማናቸውም ጊዜ ሊሰጡ ይገባል፡፡

## 9.7. የምዘና ስርዓት

9.7.1. ተቋሙ የተማሪዎች የበይነ መረብ መስመር ፈተና አዘገጃጀት፣ ምዘናና የፈተና አስተዳደር እና የፈተና እርማትና ውጤት ጥንቅር የሥራ ክፍል የአሠራር ሥርዓትና የፈተና ባንክ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤

9.7.2. ለእያንዳንዱ ኮርስ መመሪያን ወይም ማንዋልን በተከተለ መልኩ አሳይንመንት፣ ፕሮጀክት ወርክ፣ ራስን መገምገሚያ ጥያቄና የምዘና ፈተና ሊዘጋጅለት ይገባል፤

9.7.3. የስርአተ ትምህርት አዘጋጁ፣ ፈተና አውጭው እና ፈተና አራሚ አካላት የፈተናውን አጠቃላይ ሂደት እና የፈተናውን ውጤታማነት የሚከታተሉበትና የምዘና ይዘቱንና ሂደቱን የሚገመግሙበት ስርአት ሊዘረጉ ይገባል፤

9.7.4. ተማሪዎ ች በተከታታይ ምዘና፣ በአሳይንመንት እና በፕሮጀክት እንዲሁም የማጠቃለያ ፈተና ሲፈተኑ ውጤታቸው በአግባቡ ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፤ ተማሪዎች በየኮርሱ መጨረሻ ላይ የማጠቃለያ ፈተና ስርአተ ትምህርቱ ላይ በሚቀመጠው መሰረት ሁሉንም የኮርሱን ይዘቶች ባካተተ መልኩ መመዘን ይኖርባቸዋል፣

9.7.5. የፈተናው ሚስጥራዊነትና ደህንነት የተጠበቀ ሆኖ ፈተና በበይነ መረብ መስመር የሚሰጥ ሆኖ ተቋሙ የተፈታኞችን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥበት አስተማማኝ የቴክኖሎጂ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤

9.7.6. የውጤት አሰጣጡ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የመተዳደሪያ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም ይኖርበታል፤

9.7.7. የእያንዳንዱ ተማሪ ውጤት የሚቀጥለው የትምህርት ሰሚስተር ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ሊገለጽ ይገባል።

## 9.8. ቢሮዎችና የተቋሙ ፊዚካል ግብዓቶች

9.8.1. የተቋሙ ኃላፊ፣ የትምህርት ክፍል አስተባባሪዎች፣ የቅምራዊ ይዘት ዝግጅት ክፍል አስተባባሪ፣ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ አስተዳዳሪ፣ የምዘናና የፈተና ክፍል ኃላፊ፣



Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት ኃላፊ፣ የውስጥ ጥራት ማረጋገጥ አገልግሎት ኃላፊ፣ የጥናትና ምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ኃላፊ፣ ሬጅስትራርንና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች አገልግሎት የሚሰጡበት ቢሮዎች ሊኖሯቸው ይገባል፤

9.8.2. ተቋሙ ለቋሚና ተጋባዥ መምህራን ለማረፊያና የበይነ መረብ መስምር ትምህርት ዝግጅት ለማድረግ የሚያገለግሉ በሮዎች እና ትምህርት ለመስጠት የሚችሉባቸውን ቢሮዎችን እንደየትምህርት ክፍሎች ብዛትና ደረጃ ሊያደራጅ ይገባል፤

9.8.3. ቢሮዎች በተገቢው ቁሳቁስ (ወንበርና ጠረጴዛ፣ ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር፣ ስካነር፣ ስልክ፣ ፋክስ እና ኢንተርኔት) የተደራጁ መሆን አለባቸው፤

9.8.4. ከተቋሙ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ በተጨማሪ ተማሪዎች ከተቋሙ ጋር የሚገናኙበት የመስመር ስልክ፣ የፋክስ፣ የፖስታ፣ በተቋሙ ስም የተከፈተ ኢሜይል ወ.ዘ.ተ ሊኖሯቸው ይገባል፤

9.8.5. የበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ አስተማማኝ ከሆነ የኃይል አቅርቦት ጋር የሚገናኝ ሆኖ መብራት በሚቋረጥበት ወቅት ኃይል ሊያገኝ የሚችልበት አማራጭ የኃይል አቅርቦት ሊኖረው ይገባል።

## 9.9. **ተቋማዊ ሰነዶች**

9.9.1. የተቋሙን ዋና ዋና የሥራ ክፍሎች፣ የተለያያዩ ኮሚቴዎች እና የሥራ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት በአጠቃላይ የተቋሙን አሠራር፣ አመራርና ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት የሚመራበት ህገደንብ ሊኖረው ይገባል፤

9.9.2. ተቋሙ የበይነ መረብ መስመር ትምህርት ተማሪዎች የድጋፍ አገልግሎት የሚያገኙበትና እንደ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ እና የአካዳሚክ ምክር አገልግሎት ሥራዎች የሚመሩበትና የሚተገበሩበት ማኑዋል ሊኖረው ይገባል፤

9.9.3. ተቋሙ የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የምልመላና ቅጥር፣ የስልጠናና እድገት፣ የግምገማና ስንብት እና መብትና ግዴታ ወዘተ ሥርዓት የሚመራበት ማኑዋል ሊኖረው ይገባል፤

9.9.4. የአካዳሚክ ህገ-ደንቡ የተማሪ ቅበላን፣ ምዝገባን፣ መልሶ መቀበልን፣ የትምህርት ጊዜን፣ ኮርሶችን፣ የሴሚስተር ጫናን፣ ምዘናንና ለምረቃ የሚያበቁ ሁኔታዎችን ሊያካትት ይገባል፣

9.9.5. ተቋሙ የተማሪ ክፍያንና የተመላሽ ገንዘብ አመላለስ ስርዓትን ያካተተ መመሪያ ሊኖረው ይገባል፣

9.9.6. ተቋሙ የተማሪዎች መብትና ግዴታን የያዘ የተማሪዎች ሰነድ (ሀንድ ቡክ) ሊኖረው ይገባል፤

9.9.7. ተቋሙ የመምህራን ሙያዊ ስነ ምግባር መመሪያ ማንዋል ሊኖረው ይገባል፤

9.9.8. ተቋሙ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የሚያወጣቸው ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ፖሊሲዎችና ሌሎች ሰነዶች ሊኖሩትና ተፈጻሚ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፤

9.9.9. ተቋሙ መረጃ የመቀበያና የማስተላለፍያ ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል፤

9.9.10. ተቋሙ የራሱን የአምስት አመት ስትራቴጅክ እቅድና አመታዊ እቅድ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

9.9.11. ተቋሙ የመረጃ ደሕንነት ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል፤

## 9.10. የተማሪ ቅበላና ሬጅስትራር

9.10.1. ተቋሙ የሬጅሰትራር አሠራር ሥርዓት፣ የተማሪዎች ቅበላ፣ የውጤት አመዘጋገብና አገላለጽ ሥርዓት፣ የምረቃና የትምህርት መረጃ ዝግጅት፣ በሬጅስትራሩ ሥር የሚኖሩ የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን ተግባርና ኃላፊነት የሚገልጽና ጠቅላላ የሥራ ክፍል ዝርዝር አሠራሮች የሚመሩበት ማኑዋል ሊኖረው ይገባል፤

9.10.2. ተቋሙ ተገቢው የሙያ ዘርፍና ልምድ ያለው ዋና ሬጅስትራርና የሬጅስትራር ሙያተኞች ሊኖሩት ይገባል፤

9.10.3. ተቋሙ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በየዓመቱ የሚያወጣውን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መስፈርት ማእከል አድርጎ የተዘጋጀ የተማሪ ቅበላ መመሪያ፣ ሌሎች አስፈላጊ ማንዋሎችና የማስፈጸሚያ ቅጻቅጾች ሊኖሩት ይገባል፤

9.10.4. ተቋሙ የተማሪ ምዝገባና ቅበላ ከማካናወኑ በፊት ተማሪዎች በበይነ መረብ መስመር

የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ለመማር ብቁና ዝግጁ ስለመሆናቸውና ስለሚያስፈልጋቸው አነስተኛ የቴክኖሎጂ ክህሎት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ፍላጎት ማሟላት ስለመቻላቸው በዝርዝርና በይዘት ሊነግራቸውና ስምምነታቸውን እንዲገልጹ ሊያደረግ ይገባል፤

9.10.5. ተቋሙ ተማሪዎች የበይነ መረብ መስመር ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት በበይነ መረብ መስመር ትምህርት አሰጣጥ ላይ ተገቢ ገለፃ (ኦርየንቴሽን) ሊሰጣቸው ይገባል፤

## 9.11. ውስጣዊ የጥራት ማረጋገጥ ሥርዓት

9.11.1. ተቋሙ የኤጀንሲውን አስር የትኩረት መስኮች በመከተልና የበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን ታሳቢ ባደረገ አግባብ የተዘጋጀ የውስጥ ጥራት ማስጠበቂያ መመሪያ ወይም ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል፤

9.11.2. ተቋሙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልምድ ያለውና ስለውስጥ ጥራት አጠባበቅና የበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በቂ ዝግጅት ያደረገ ባለሙያ ሊመድብ ይገባል፤

9.11.3. ተቋሙ ባለሙያው ኮምፒውተር፣ ሸልፍ፣ ወንበር፣ ጠረጴዛና ሌሎች የቢሮ ቁሳቁሶች የተሟላለት የመስሪያ ቦታ እንዲኖረው ማድረግ ይገባል፤

9.11.4. ተቋሙ ከተማሪዎች ማመልከቻ ጀምሮ ያሉትን አጠቃላይ የተቋሙን ስራዎች በመከታተል የሚገመግምበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፤

9.11.5. ተቋሙ መመሪያውን ወይም ፖለሲውን ተከትሎ የክፍሉን እቅድ ማዘጋጀትና በቂ በጀት መመደብ ይኖርበታል።

## 9.12. የጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት

9.12.1. ተቋሙ የጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን የበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን ባማከለ መልኩ በአግባቡ ለመምራት በሚያስችል የተዘጋጀ መመሪያ ወይም ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል፤

9.12.2. ተቋሙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ልምድ ያለውና የጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎትና የበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ላይ በቂ ዝግጅት ያደረገ ባለሙያ ሊኖረው ይገባል፤

9.12.3. ተቋሙ ለባሙያው ኮምፒውተር፣ ሸልፍ፣ ወንበር፣ ጠረጴዛና ሌሎች የቢሮ ቁሳቁሶች የተሟላለት የመሥሪያ ቦታ ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

9.12.4.ተቋሙ መመሪያውን ወይም ፖሊሲውን ተከትሎ የክፍሉን እቅድ ማዘጋጀትና በቂ በጀት መመደብ ይኖርበታል።

## 10. የዕውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

10.1. ኤጀንሲው ከ9.1 እስከ 9.12 የተቀመጡ መሰረታዊ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ገምግሞ በማረጋገጥ ለ3 ዓመት የሚያገለግል የዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል።

10.2. የዕውቅና ፈቃድ የተከለከለ ተቋም ክልከላው ከተገለፀበት ቀን አንስቶ በ**90** ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን መመዘኛዎች በማሟላት እንደገና ማመልከት ይችላል። የእውቅና ፈቃድ በድጋሚ የተከለከለ ተቋም ደግሞ ከተከለከለበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ በድጋሚ ሊያመለክት ይችላል።

# ክፍል አራት
# የዕውቅና ፈቃድ ስለማደስ

## 11. የመገምገሚያ መስፈርቶች

በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት በበይነ መረብ መስመር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ትምህርት ሲሰጥ የቆየ ተቋም የእውቅና ፈቃድ ጊዜው ሲጠናቀቅ ተማሪዎችን በቀጣይነት ተቀብሎ ማስተማር የሚችለው የሚከተሉት መሰረታዊ የጥራት መለኪያ መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ስለመሟላቱ በኤጀንሲው ሲረጋገጥና የእውቅናው ፈቃድ ሲታደስለት ብቻ ነው።

### 11.1. ህንጻና አካባቢያዊ ሁኔታ

በአንቀፅ **9** ንዑስ አንቀፅ **9.1** ስር የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተቋሙ እውቅና ባገኘበት ህንጻ ላይ ስለመሆኑ ወይም የህንጻ ለውጥ ያደረገ ከሆነ ለኤጀንሲው አቅርቦ

ስለመፈቀዱ ማረጋገጥ እና በህንጻው ላይ ያደረጋቸው ለውጦችን/መሻሻሎችን የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

## 11.2. አመራርና አደረጃጀት

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.2 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተቋሙ በአደረጃጀቱ ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች/መሻሻሎች የያዘና የመምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የቅጥርና እድገት መመዘኛዎች እና አተገባበራቸው ላይ ሪፖርት ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል።

## 11.3. ስርዓተ ትምህርት

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.3 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተቋሙ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት ያከናወነውን የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፤ በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ ያከናወነውን ግምገማና ያሳተፋቸውን የባለድርሻ አካላት እንዲሁም ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

## 11.4. ቅምራዊ የማስተማር ስነዘዴ ነደፋ (Digital Instructional Design)

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.4 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በቅምራዊ ይዘት ዝግጅትና አተገባበር ላይ ያጋጠሙትን ችግሮች እና የወሰዳቸውን የመፍትሄ ሀሳቦችና እንዲሁም በኮርስ ደረጃ የተከናወኑ ግምገማዎችንና ያደረጋቸውን ማሻሻያዎች የያዘ ሪፖርት ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል።

## 11.5. የትምህርት አስተዳደር ስርዓት (Learning Management System)ና የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.5 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተቋሙ በትምህርት አስተዳደር ስርዓት አተገባበር፣ ያጋጠመውን ችግር፣ የተወሰደ መፍትሔና በአጠቃላይ በስርዓቱ ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል። በተጨማሪም ስርዓቱን በመጠቀም መማር ማስተማሩ የተከናወነበትን ሁኔታ መምህራንና ተማሪዎች የነበራቸውን ግብረመልስ ማካተት ይኖርበታል።

## 11.6. **የመምህራንና የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት**

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.6 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተቋሙ በመምህራንና በተማሪዎች አገልግሎት ድጋፍ ላይ ስላደረጋቸው ለውጦችና ክንውኖች ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል። ሪፖርቱ የመምህራን የማስተማር ሂደት፣ የግምገማ ውጤትና የተወሰደ መፍትሄ፤ ለመምህራን ስለተሰጠ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና፣ ተማሪዎች ላሉባቸው ችግሮች የተሰጠ ምላሽና መፍትሄ በዝርዝር ሊይዝ ይገባል። በተጨማሪም የእውቅና ፍቃድ በሚታደስበት ወቅት የቋሚና ጊዜያዊ መምህራን ጥመርታ 30:70 ሊሆን ይገባል።

## 11.7. **የምዘና ስርዓት**

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.7 ሥር የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተቋሙ በፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ላይ ያለውን አፈጻጸም የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል። የፈተናዎች አዘገጃጀትና የፈተና አስተዳደር ስርዓት ቀደም ሲል እውቅና በተሰጠበት ወቅት በተዘረጋው ስርዓት መሰረት መፈጸም አለበት።

## 11.8. **ቢሮዎችና የተቋሙ ፊዚካል ግብዓቶች**

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.8 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተቋሙ በቢሮዎችና በፊዚካል ግብዓቶች ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል። ተቋሙ እውቅና በተሰጠበት አግባብ ክፍሎች እራሳቸውን ችለው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ በሚያስችላቸው አግባብ በቢሮዎች ላይ ማሻሻያ ማድረግ አለበት።

## 11.9. **ተቋማዊ ሰነዶች**

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.9 ሥር የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በተቋሙ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና ሌሎች ተቋማዊ ሰነዶች ላይ በየጊዜው ከተቋሙ እድገትና ነባራዊ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ማሻሻያ ስለመደረጉ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

## 11.10. **የተማሪ ቅበላና ሬጅስትራር**

በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.10 ስር የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተቋሙ ተማሪዎችን የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን የመግቢያ መስፈርት ተከትሎ መመዝገቡ፣

ለተማሪዎች አስፈላጊውን ኦሪየንቴሽን መስጠቱ፣ የተማሪዎችን ፋይል ከአስፈላጊ ግብዓት ጋር ባግባቡ መያዙና ተቋሙ በተፈቀደለት የተማሪ ቅበላ መጠን ስለመቀበሉ ለኤጀንሲው ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

## 11.11. የውስጥ የጥራት ማረጋገጥ ሥርዓት

በአንቀፅ **9** ንዑስ አንቀፅ **9.11** የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የውስጥ ጥራት ማረጋገጫ ዩኒት ተቋሙ የሚሰጠውን ትምህርት አግባብነትንና ጥራትን ከማረጋገጥ አንጻር ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል። የክፍሉ ሪፖርት በተከታታይና የሚመለከታቸውን ክፍሎች በማሳተፍ ያደረጋቸውን የዳሰሳ ጥናቶች፣ ያስቀመጣቸውን የመፍትሄ ሀሳቦችና የመጣውን ለውጥ ማካተት ይኖርበታል።

## 11.12. የጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት

በአንቀፅ **9** ንዑስ አንቀፅ **9.12** ሥር የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የመመረቂያ ጽሑፍ ወይም የፕሮጀክት ሥራ የማማከር ሂደት፣ የጥናትና ምርምር ፕሮፖዛል አዘገጃጀት፣ ግምገማና አጸዳደቅ ስርዓትና የበጀት አጠቃቀም ስርዓትና የጥናትና ምርምር ስርፀት እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ የገበያ ትስስር ስርዓት ስለመኖሩ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

## 11.13. የተደረጉ ማሻሽያዎች የስራ አፈጻጸምና የተገኘ ውጤት

11.13.1. የተደረጉ ማሻሻያዎች ተቋሙ የእውቅና ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት በቀጣይነት ማሻሻያ እንዲያደርግ በሚጠበቁበት ጉዳዮች ዙሪያ ማሻሻያ ማድረጉን ማረጋገጥ አለበት፤

11.13.2. የሂደትና የውጤት ግምገማው የተቋሙን የመማር ማስተማር ሂደት በተጨባጭ እንደሚከተለው ይገመገማል፣

- የተለያዩ አሳታፊና ተማሪ ተኮር የመማርያ ዘዴዎችን መጠቀሙ፤
- የታቀደ አካዳሚክና የማህበራዊ የማማከር ስራ መሰራቱ፤
- የኮርስ ሽፋን ሥርዓተ ትምህርቱን መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ፤
- ፈተናዎች የሚወጡበት፣ የሚገመገሙበትና የሚጸድቁበት የአስተዳደር ስርዓት

ተግባራዊ ስለመሆኑ፤

- ተከታታይ የምዘና ስርዓት ተግባራዊ ስለመሆኑ፣
- ተቋሙ የእውቅና ፈቃዱን ሲያገኝ በነበረበት አግባብ እያስተማረ ስለመሆኑ፤
- ያከናወናቸው ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራና ሽግግሮች እና የታተሙ ጽሑፎችና መሰረት በማድረግ ይገመገማሉ።

## 12. የብቃት ማረጋገጫ/የመውጫ ፈተና ስለመስጠት

በበይነ መረብ መስመር የሚሰጠውን ትምህርት የሚያጠናቅቁ ተመራቂ ተማሪዎች የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት የሚያዘጋጀውን የብቃት ማረጋገጫ ፈተና በመውሰድ ወደ ስራ ዓለም ለመቃለቀል የሚያስችላቸውን እውቀትና ክህሎት መላበሳቸውን የሚረጋገጥ ይሆናል።

## 13. የእውቅና ፈቃድ እድሳት ስለመስጠት

13.1. በአንቀጽ **11.1** እስከ **11.13** የተዘረዘሩት በሙሉ መሟላታቸውን በማረጋገጥ ኤጀንሲው እንደ ፕሮግራሙ ቆይታ ከ3-5 ዓመት የሚያገለግል የእውቅና ፈቃድ እድሳት ይሰጣል፤

13.2. የእውቅና ፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም በኤጀንሲው የተገለፁትን ተፈላጊ መመዘኛዎችን አሟልቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንደገና ማመልከት ይቻላል፤ ዳግም የእውቅና ፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም የተቀበላቸውን ተማሪዎች የእውቅና ፈቃድ ባላቸው ሌሎች ተቋማት ተዘውረው ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል። ነገር ግን የትምህርት መስኩ በሌላ ተቋማ የማይሰጥ ከሆነ ተቋሙ ያለበትን የጥራት ክፍተት በማስተካከል ተማሪወቹን የሚያስጨርስበት ሁኔታ የሚታይ ይሆናል።

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 14. ጥቆማ

14.1. ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ መርሆዎችን የሚጻረር ጥፋት መፈጸሙን በማንኛውም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፤ ኤጀንሲው ለሚቀርብለት ጥቆማ የሚያስተናግድበትን ስርዓት በመዘርጋት



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Science and Higher Education

በተቋማት የስነስርዓት መመሪያ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

14.2. ኤጀንሲው የጥቆማ አቅራቢውን ሚስጥራዊነትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 15. የመተባበር ግዴታ

15.1. ተቋማት ኤጀንሲው የሚፈልገውንና የሚጠይቀውን መረጃና ሌላ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፤ ይህም የሁለቱም አካላት መብትና ግዴታን በተመለከተ በሚዘጋጀው ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡

15.2. ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በሚደረጉ ህጋዊ እንቅስቃሴዎች የክልል መስተዳድሮች ፤ የፍትህ አካላት ፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችና ወላጆች እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 16. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፤ የአስተዳደር ውሳኔ፤ የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 17. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡